«የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።» 2ጢሞ. 3፥16-17




«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤
ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።»
መዝ. 118(119)፥130

**Global Good News Literature**
**የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት**
**P.O.BOX 451336**
**Los Angeles, CA 90045**
email: info@globalgoodnews.org
**Copyright © 2008**



## ማውጫ

ክፍል ፩

| | ገጽ |
|---|---|
| ትምህርት ዘጠኝ፡- ሥላሴ ........ | 5 |
| የእግዚአብሔር ባሕርይ ........ | 5 |
| የእግዚአብሔር የሀልውና ባሕርይ ........ | 5 |
| የእግዚአብሔር አንድነት ........ | 6 |
| በአንዱ እግዚአብሔር ያለ ሦስትነት | 6 |
| እግዚአብሔር አብ ........ | 7 |
| እግዚአብሔር ወልድ ........ | 8 |
| እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ........ | 8 |
| የትምህርተ ሥላሴ መግለጫ ........ | 9 |
| ትምህርት ዘጠኝ፡- ሥላሴ - ጥያቄዎች ........ | 11 |

## <u>የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት</u>
## <u>የመላላክ ትምህርት</u>

የዚህ የመላላክ ትምህርት ዋና ዐላማ በጌታ ዐዲስ ለሆኑ፣ እንዲሁም በጌታ ከሆኑ ቈየት ቢሉም፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ለሚፈልጉ ወንድሞችና እኅቶች መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ለማስተማርና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት ነው። «ፈረስን ወደ ውሃ ታመጣዋለህ እንጂ እንዲጠጣ አታስገድደውም» እንደሚባለው ሁሉ፣ እነዚህ ትምህርቶች ተማሪው በትጋት ካልተከታተላቸውና በውስጣቸው ያሉትንም ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያመሳከረ በሚገባ ካላጠና፣ እንዲሁ በአንድ ጊዜ ንባብ ብቻ የሚፈለገውን ውጤት ያስገኛሉ ማለት አዳጋች ነው። ስለዚህ ይህንን ትምህርት የምትከታተሉትን ሁሉ፣ እያንዳንዱን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አውጥታችሁ ጥቅሶቹን በማመሳከር በትጋት፣ እንድታጠኑት እናበረታታለን።

እነዚህን ትምህርቶች በግልም ሆነ በኅብረት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ መጠቀም ይቻላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጀማሪዎችን የማስተማር ኀላፊነት ያለበት ሰውም ሌሎችን ለማስተማር ሊጠቀምባቸው ይችላል። ትምህርቶቹን በእኛ በኩል በግል ለመከታተል የምትፈልጉ ግን በመጀመሪያ መመዝገብና የመታወቂያ ቍጥር መቀበል ይኖርባችኋል። ከዚያም ከእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ ላሉት ጥያቄዎች በቂ መልስ በመላክ የመላላኩን ትምህርት መቀጠል ትችላላችሁ።

የመላላክ ትምህርቱ፣ ዐሥራ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ትምህርቶችን ያካተተ ሲሆን፣ አራት አራቱን ከፋፍለን በሦስት ክፍሎች አቅርበናቸዋል። አርእስቱ፣ ለአንድ ክርስቲያን ያስፈልጋሉ ብለን ያመንባቸው አርእስት ናቸው። ትምህርቶቹን በጥሞናና በረጋ መንፈስ አጥንታችሁ ከትምህርቱ ጋር የተገናዘበ በቂ መልስ እንጂ በችኰላ የቸልተኝነት ወይም ከትምህርቱ ጋር የማይዛመድ መልስ እንዳትሰጡ ልናሳስብ እንወዳለን።

ትምህርቶቹን በደንብ አጥንታችሁ የጥያቄዎቹን መልስ፣ በየክፍሉ ያሉትን አራት አራት ትምህርቶች በየተራ፣ ወይም የዐሥራ ሁለቱንም ትምህርቶች በአንድነት ስትልኩልን፣ መልሳችሁን አይተን ይህንን የመላላክ ትምህርት እንደ ጨረሳችሁ የሚገልጽ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት እንልክላችኋለን።





# ክፍል ፩



**«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤**
**ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።»**
**መዝ. 118(119)፥130**

## <u>ትምህርት ዘጠኝ፡- ሥላሴ</u>

የሰው አእምሮ በጊዜ፣ በቦታ፣ በመረዳትና በማገናዘብ ዐቅሙ እጅግ የተወሰነ በመሆኑ፣ ስለ እግዚአብሔር ማንነት ሙሉ ለሙሉ መረዳት አይችልም። ትምህርተ ሥላሴ ሰው ሌላውን ዕውቀት በሚረዳበት አስተሳሰብ እንደዚህና እንደዚያ ነው በሚል ትንታኔ ሊገነዘበው የሚቻል አይደለም። ምስጢረ ሥላሴ ሙሉ ለሙሉ ከመታወቅ በላይ ነው።

የእግዚአብሔርን ማንነት ለመግለጽ መሞከር ቀላል አይሆንም። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ በገለጸውና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በተረዳነው መጠን ስለ ማንነቱ መናገር ይቻላል።

<u>«ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው</u>፤ የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው።» (ዘዳ. 29፥29)

### <u>የእግዚአብሔር ባሕርይ</u>

1. ቅዱስ ነው (ዘሌ. 19፥2፤ 1ጴጥ. 1፥15)።
2. ጻድቅና ቅን ፈራጅ ነው (መዝ. 119፥137)።
3. እውነተኛና ታማኝ ነው (ዮሐ. 17፥3፤ ቲቶ 1፥1-2፤ ዘዳ. 7፥9፤ መዝ. 89፥1-2)።
4. መሓሪና ቸር ነው (መዝ. 103፥8-17፤ 111፥4)።
5. ፍቅር ነው (ዮሐ. 3፥16፤ ሮሜ 5፥8፤ 1ዮሐ. 4፥7-10)።
6. ጠቢብ ነው (ምሳ. 3፥19፤ ኢሳ. 40፥28)።

### <u>የእግዚአብሔር የህልውና ባሕርይ</u>

1. ያለማንም ሠሪ ራሱ በራሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚኖር ነው (ዘጸ. 3፥13-14)።
2. በራሱ ብቁ የሆነ አምላክ ነው (መዝ. 50፥10-12፤ ኢሳ. 40፥13-14)።
3. ዘላለማዊ ነው (ዘዳ. 33፥27፤ መዝ. 90፥2፤ ኢሳ. 40፥28)።
4. በቦታ፣ በችሎታና በዕውቀት ያልተወሰነ ነው (1ነገ. 8፥27፤ ኤር. 23፥24፤ ኢሳ. 40፥12-26፤ መዝ. 139፥2-12፤ ዘፍ. 18፥14፤ ራእ. 19፥6)።
5. ብቻውን ታላቅ አምላክ ነው (ኢሳ. 44፥24፤ 46፥9፤ 1ጢሞ. 1፥17)።
6. መንፈስ ነው (ዮሐ. 4፥24)።
7. አንድም ሦስትም ነው (ዘዳ. 6፥4-5፤ ማቴ. 28፥19፤ 2ቆሮ. 13፥14)።





### <u>የእግዚአብሔር አንድነት</u>

እግዚአብሔር አንድ ነው። አንድ አምላክ ብቻ አለን። «እስራኤል ሆይ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው። አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹምም ነፍስህ፣ በፍጹምም ኀይልህ ውደድ።» (ዘዳ. 6፥4) በተጨማሪ የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ (1ቆሮ. 8፥4፤ 1ጢሞ. 2፥5፤ ኤፌ. 4፥6፤ ዮሐ. 10፥30)።

እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ቃል ኪዳን ዐስቦ እስራኤልን ከግብጽ ምድር ካወጣ በኋላ፣ በሲና ምድረ በዳ በሙሴ በኩል ለእስራኤል የሰጠው የመጀመሪያው ሕግ፣ «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» (ዘጸ. 20፥3) የሚል ነው። ግብጻውያንም ሆኑ በከነዓንና በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ብዙ አማልክትን ይከተሉ ስለ ነበር፣ የእስራኤላውያን መጠራት ዋና ዐላማ አምላካቸው እግዚአብሔር መሆኑን እንዲመሰክሩና አሕዛብ ሁሉ ይህን አንድ አምላክ እንዲያውቁና እንዲያመልኩ ነው። እግዚአብሔር ከአማልክት ሁሉ በላይ የሆነ አምላክ ነው (2ዜና. 2፥5)።

### <u>በአንዱ እግዚአብሔር ያለ ሦስትነት</u>

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን የሚታወቀው በአጠቃላይ በአንድነቱ ነው። የአካል ሦስትነቱ የተገለጸው ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር ከመጣ በኋላ ነው። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከአንድ በላይ ሆኖ የተጠቀሰባቸው በርከት ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ።

### <u>እግዚአብሔር ከአንድ በላይ በሆነ ቍጥር ራሱን የገለጸባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች</u>

1. «እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤» (ዘፍ. 1፥26)

2. «እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤ ...» (ዘፍ. 3፥22)

3. «እግዚአብሔርም አለ፡- ... ኑ፤ እንውረድ፤ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው።» (ዘፍ. 11፥6፡7)

### <u>ሦስትነትን የሚያሳዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች</u>

4. «ወደ እኔ ቅረቡ፤ ይህንም ስሙ፤ እኔ ከጥንት ጀምሬ በስውር አልተናገርሁም፤ ከሆነበት ዘመን ጀምሮ <u>እኔ በዚያ ነበርሁ፤</u> አሁንም <u>ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ</u> ልከውኛል።» (ኢሳ. 48፥16) ከቍጥር 12 ጀምሮ ብናነበው «<u>እኔ</u>» የሚለው፣ ኢሳይያስ ሳይሆን ከሥላሴ አካላት አንዱ እንደ ሆነ እንረዳለን። «<u>ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ</u>» ሲል ደግሞ ሁለቱን የሥላሴ አካላት (አብንና መንፈስ ቅዱስን) ማመልከቱ ነው።

5. «ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሃ ወጣ፤ እነሆም፣ ሰማያት ተከፈቱ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ፣ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም፣ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ፡- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ፡፡» (ማቴ. 3፥16-17) በዚህ ክፍል ወልድ ሲጠመቅ፣ መንፈስ ቅዱስ በአካል መልክ ሲወርድ፣ አብ ደግሞ ሲናገር እንሰማለን፡፡

6. «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ <u>በአብ፣ በወልድና</u> በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው…» (ማቴ. 28፥19)

7. «የጌታ የኢየሱስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡» (2ቆሮ. 13፥14) ይህ ጥቅስ ፡-

   ሀ. አብ እንደ ወደደን፣
   «እግዚአብሔር (አብ) አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐ. 3፥16)

   ለ. ክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋን እንዳቀዳጀን፣
   «ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ ዐደረ … ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበረና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ፡፡» (ዮሐ. 1፥14 እና 17)

   ሐ. መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከአማኞች ጋር ኅብረትን እንደሚሰጠን ያስተምረናል፡፡
   «እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠ ምቀናልና፡፡ ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል፡፡» (1ቆሮ. 12፥13)

<u>እግዚአብሔር አብ</u>

«ከገናናው ክብር በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ድምፅ በመጣለት ጊዜ <u>ከእግዚአብሔር አብ</u> ክብርንና ምስጋናን ተቀብሎአልና፡፡» 2ጴጥ. 1፥17

«በእርሱ (በክርስቶስ ኢየሱስ) የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ፣ እግዚአብሔር (አብ) አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡» (ዮሐ. 3፥16)

እነዚህን ጥቅሶችና ሌሎችንም ስንመለከት፣ አብ፡-

1. የፍጥረት ሁሉ አባትና ተቈጣጣሪ ነው፡፡
2. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነው፡፡
3. አንድያ ልጁን ስለ ኀጢአታችን ሲል አሳልፎ የሰጠን ነው፡፡





<u>እግዚአብሔር ወልድ</u>

እግዚአብሔር ወልድ (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ) ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለድ ሥጋ ለብሶ ሰውን ለማዳን ወደ ዐለም በመምጣት የመጣበትን ተልእኮ እስከ መስቀል ሞት ድረስ በመታዘዝ የፈጸመ፣ በኋላም በሦስተኛው ቀን ከሞት የተነሣና ወደ ሰማይ ዐርጎ በአብ ቀኝ የተቀመጠ መለኮት ነው፡፡

ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ በጻፈው ወንጌል፣ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበር፡፡ ይህ በጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡፡ ሁሉ በእርሱ ሆነ፡፡ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም፡፡ … ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ ዐደረ፡፡» (ዮሐ. 1፥1-3፡14)

«ይህም ጸጋ ኀጢአተኛነትንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም <u>የታላቁን የአምላካችንንና የመድኀኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር</u> መገለጥ እየጠበቅን … እንድንኖር ያስተምረናል» (ቲቶ 2፥13)፡፡ ይህ ጥቅስ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ (ወልድ) ታላቅ አምላክ እንደ ሆነ በግልጽ ይናገራል፡፡

ይህ ጌታ ፍጹም ሰው ቢሆንም፣ በመጀመሪያ የነበረ ፍጹም እግዚአብሔርም ነው፡፡ «እርሱ (ወልድ) በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠ ረውም» (ፊል. 2፥6)፡፡

«እርሱም (ወልድ) የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም፣ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፣ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና» (ቈላ. 1፥15-17)፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ መጠራቱ፣ ከአብ ጋር ያለውን ግንኙነት /Relationship/ ለመግለጽ እንጂ ወልድ በአብ ተፈጠ ረ ለማለት ወይም ወልድ ጅማሬ እንዳለው የሚያመለክት ቃል አይደለም፡፡

<u>እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ</u>

ክርስቶስ ከሞት በተነሣ በኀምሳኛው ቀን (በጰንጠቆስጤ ቀን ሐዋ. 2፥1) ወደ ዓለም የመጣውና ደቀ መዛሙርትን በኀይል የሞላው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በምድር እየሠራ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ከሚያደርጋቸው ውስጥ አንዳንዶቹ፡-

- ያስተምረናል (ዮሐ. 14፥26ሀ)፤
- ክርስቶስን ያከብራል (ዮሐ. 16፥14)፤

- ለአማኞች ኀይልን ይሰጣል (ሐዋ. 1÷8)፤
- ዓለምን ስለ ኀጢአት ይወቅሣል (ዮሐ. 16÷8)፤
- እውነትን ያሳስባል፤ (ዮሐ. 14÷26ለ)፤
- ያጽናናል፤ ዮሐ. (14÷16 እና 26)፤
- የአብና የወልድ የሆነውን ለአማኞች ይሰጣል (ዮሐ. 16÷14-15)::

ብዙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ኀይል ብቻ እነደ ሆነ ተደርጎ ይወሰዳል:: ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ህልውና ያለው መለኮት ነው:: ስለሆነም:-

1. የሰውን ሐሳብ ይመረምራል (ሮሜ 8÷27፤ 1ቆሮ 2÷10)::
2. ፈቃድ አለው (ይከለክላል፤ ይመራል፣ ይናገራል፤ ይጸልያል)::
3. ስሜት (አለው ይወዳል፤ ያዝናል) (ሮሜ 15÷30፤ ኤፌ. 4÷30)::

የእግዚአብሔር ቃል መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ሲናገር፣ «ጴጥሮስም፣ ሐናንያ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን ስለምን በልብህ ሞላ? .... እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም» (ሐዋ. 5÷3-4) ይላል::

## የትምህርተ ሥላሴ መግለጫ

1. አንድ የማይከፈል አምላክ አለ:: እግዚአብሔር በመለኮትም፣ በባሕርይም አንድ ነው (ዘዳ. 6÷4)::

2. በአንዱ አምላክ ሦስት አካላት (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ) አሉ:: አካል የሚለው ቃል የሥላሴን ህልውና በበቂ ሁኔታ ሊገልጽ አይችልም:: ምክንያቱም አካል /person/ የሚለው ቃል ለሰው ሲውል የተለያዩና አንድ ያልሆኑ ሰዎችን ሊያመለክት ስለሚችል ነው:: የእግዚአብሔር አካላዊ ሦስትነት ግን በአካልነት የተለያየ ማንነትን የሚያሳይ ቢሆንም፣ አንድ አምላክነትን የሚያመለክት ልዩ (ቅድስት) ሦስትነት ነው:: እግዚአብሔር በባሕርይ ብቻ ሳይሆን፣ በመለኮትም አንድ ነው::

3. የእግዚአብሔር ያልተከፈለና ያልተቀነሰ እርሱነቱ በሙላት ለሁሉም (ለአብ፣ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ) እኩል አላቸው:: ሦስቱም እኩልና ፍጹም ስለ ሆኑ፣ አንደኛው ከሌላው ሊበልጥ ወይም ሊያንስ አይችልም:: ስለሆነም ሦስቱም እኩል ክብር አላቸው::

4. አብ ዓለምን እንዲሁ ወድዶ አንድያ ልጁን (ወልድን) ሰጠ (ዮሐ. 3÷16):: ወልድ እንደ መልካም እረኛ ነፍሱን ለበጎቹ አሳልፎ ሰጠ (ዮሐ. 10÷11):: መንፈስ ቅዱስ ሰዎች በኀጢአታቸው ተጸጽተው ወደ ወልድና ወደ አብ እንዲመለሱ ሰዎችን በመውቀሥ ዳግመኛ እንዲወለዱ ያደርጋል (ዮሐ. 16÷8፤ ቲቶ 3÷5)::





5. ስለ ምስጢረ ሥላሴ (ሦስትነትና አንድነት) በመጠኑ የሚገልጹ ምሳሌያዊ አገላለጾች አሉ::

    ሀ. ዛፍ:- የዛፉ ሥር፣ ግንድ፣ ቅርንጫፍ፣

    ለ. ፀሓይ:- የፀሓይ አካል፣ ብርሃን፣ ሙቀት፣

    ሐ. ውሃ:- ፈሳሽ፣ እንፋሎት፣ በረዶ::

እነዚህ አገላለጾች ስለ ምስጢረ ሥላሴ ለመረዳት መጠነኛ ፍንጭ የሚሰጡ ቢሆንም፣ የእግዚአብሔርን ማንነት አሟልተው ሊገልጹ አይችሉም:: እግዚአብሔርን በየትኛውም ምሳሌ መመሰል ትክክል አይሆንም::

**«እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ?**
**ወይስ በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ?» (ኢሳ. 40÷18)**

## ትምህርት ዘጠኝ፦ ሥላሴ

የመታወቂያ ቁጥር፣ ______________________________
ስም፤ ______________________________
አድራሻ፤ ______________________________
______________________________
______________________________

1. የእግዚአብሔርን ባሕርያት ከጠቀስህ በኋላ ስለ አንዱ አብራራ።

2. የእግዚአብሔርን የህልውና ባሕርያት ከገለጽህ በኋላ አንዱንራራ።

3. እግዚአብሔር በመለኮት አንድ ነው፤ በአካል ግን ሦስት ነው የሚለውን እውነት እንዴት ትረዳዋለህ?

4. የእግዚአብሔር ሦስት የአካል ስያሜዎች ምን ምን ናቸው?

5. እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ምን ምን በማድረግ ይታወቃሉ? የሦስቱንም ድርሻ በተናጠል አስረዳ።

6. በአንዳንድ የሐዋርያት መልእክቶች መጨረሻ ላይ (ለምሳሌ 2ቆሮ. 13፥14)፣ «የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ (የወልድ) ጸጋ የእግዚአብሔርም (የአብ) ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን።» የሚለው ቃል ለግል ሕይወትህ ምን ትርጒም አለው?